ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

ማህበራዊ ሳይንስና ስነ - ሰብ ኮሌጅ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

" በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሃፍ ከልቦለድ አላባውያን አንፃር መተንተን"

# " በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ ከልቦለድ አላባውያን አንፃር "


በ

መቅደስ ከበደ

አማካሪ

ሜሮን ተስፋዬ



ነሐሴ 2013አ/ም

" በፍቅር  ስም ልቦለድ መፅሐፍ ከልቦለድ አላባውያን አንፃር "

በ

መቅደስ ከበደ

አማካሪ

ሜሮን ተስፋዬ

ለባችለር ኦፍ አርትስ ዲግሪ ማሟያ የተሰራ

ነሐሴ 12/2013አ.ም

የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ በወልቂጤ ዩንቨርሲቲ  የቴያትር ጥበባት ት/ት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪ ማማከሪያ መስፈርት ድጋፍ የተደረገበት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪው ስም

ፊርማ

ይህ በተማሪ መቅደስ ከበደ በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሃፍ ከልቦለድ አላባውያን አንፃር በሚል ርዕስ የተሰራውን የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ፅሑፍ የዩንቨርስቲውን ጥናት ደረጃ ያሟላ ና የቴያትር  ጥበባት ት/ት ክፍል ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጫ ነው።

ይህ በፈታኝ ኮሚቴው ተረጋግጧል ።

አማካሪ ሜሮን ተስፋዬ

ፊርማ

ፈታኝ 1

ፊርማ

# ምስጋና

በመጀመሪያ አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ለድንግል ማርያም ልጅ ለልዑል እግዚአብሔር ይሁን ።በመቀጠል

ሰለቸኝ ሳትል ግዙፉ ስህተቴን አርማ ለዚህ ላበቃችኝ ለመምህርት ሜሮን ተስፋየ ከልብ አመሰግናለሁ ።

እንዲሁም እንደእናትም እንደ አባትም ሆና ለዚህ ላደረሰችኝ እነቴ እና ቤተሰቦቼ ይሁንልኝ ።በመጨረሻም ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ስሰራ መፅሐፍ እንዲሁም ሀሳብ ለለገሱኝ ሁሉ ምስጋናየን አቀርባለሁ ።

## መታሰቢያነቱ

በቅርቡ በካንሰር ህመም በሞት ላጣሁት ለአባቴ አቶ ከበደ ደምሴ ይሁንልኝ ።

## አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ ከልቦለድ አላባውያን አንፃር መተንተን ነው። ጥናቱ የተሰራበት ዘዴም ገለፃዊ ሲሆን የተጠቀመው የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ መፅሐፉ በማንበብ እና ተያያዥነት ያላቸው ፅሁፎች በማንበብ ነው።ጥናቱ የሚያነሳቸው ሀሳቦችም በፍቅር ስም ልቦለድን ከልቦለድ አላባውያን ማየትና መተንተን ነው።

ማውጫ ገጽ


ምዕራፍ አንድ........................................................................................................1

1.መግቢያ ........................................................................................................1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................................................1

1.2 የጥናቱ አላማ ........................................................................................................1

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................................................................................1

1.4 የጥናቱ ወሰን........................................................................................................2

1.5 የጥናቱ ዘዴ ........................................................................................................2

1.6 ጥናቱ የሚያሳቸዉ ጥያቄዎች........................................................................................................2

1.7 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች........................................................................................................2

1.8 የመፍትሔ ሐሳብ ........................................................................................................3

1.9 የጥናቱ አወቃቀር ........................................................................................................3

ምዕራፍ ሁለት........................................................................................................4

2 ክለሳ ድርሳናት........................................................................................................4

2..1 የልቦለድ ምንነት ........................................................................................................4

2.2 የልቦለድ አላባዉያን ........................................................................................................5

2.2.1ታሪክ ........................................................................................................5

2.2. 2 ትልም ........................................................................................................6

2.2.3 ገፀ ባህሪ........................................................................................................6

2.2.4 ግጭት ........................................................................................................7

2.2.5. መቼት 7

2.2.6 ጭብጥ 8

2.2.7. አንፃር 8

2.2.8. የልቦለድ አይነቶች 9

2.3 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት 10

ምዕራፍ ሶስት 11

3.1. በፍቅር ስም ልቦለድ መጽሐፍ አጭር ታሪክ 11

3.1. 1 በፍቅር ስም ልቦለድ ከታሪክ አንፃር 12

3.1.2 በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ ከገፀባህሪየት አሳሳል አንፃር 13

3.1.3 በ ፍቅር ስም ልቦለድ መጽሀፍ ከ መቼተ አንፃር 15

3.1.4. በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ ከጭብጥ አንፃር 16

3.1.5 በፍቅር ስም ልቦለድ ከግጭት አንፃር 17

3.1.6 በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ ከትልም አንፃር 17

3.1.7. በፍቅር ስም ልቦለድ ከአንፃር ሲታይ 18

ምዕራፍ አራት 19

4 ማጠቃለያ 19

ዋቢ መፅሐፍት 20

# ምዕራፍ አንድ

## 1.መግቢያ

ስነፅሁፍ በሰው ልጅ ታሪክ ለረጅም ዘመናት የቆየ ኪነጥበብ በመሆኑ ብዙ ሀሳቦች የተሰነዘሩበት ብዙ ክርክሮችና ምርምሮች የተደረጉበት መስክ ነው ።ስለምንነቱ ስላፈጣጠር ምስጢር ስለሚያካትታቸዉ ነገሮች በሰዎች ላይ ስለሚያሳድረዉ ተፅፅኖ ስለሚሰጠው አገልግሎት ያልተባለ ነገር የለም ። በስነፅሁፍ ስር ከሚመደቡት አንዱ ልቦለድ ነው ።ልቦለድ ማለት አንድ ደራሲ ወይም ፀሐፊ ሀሳቡን በነፃነት የተሰማውን ስሜት በሂወት ዘመኑ ሲኖር ሰዎች ላይ ያየውን ነገር በራሱም ሂወት ይችላል ያጋጠመውን ነገር ሰዎች ይማሩበታል ይዝናኑበታል ቁም ነገር ይጨብጡበታል ከተለያዩ መጥፎ ድርጊቶች ይቆጠቡበታል ብሎ ያመነውን ነገር መፅሃፍ ላይ አስፍሮ ለተደራሲያን ሲያቀርብ ነው። ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚዳስሰው በፍቅር ልቦለድ መፅሐፍን ከልቦለድ አላባውያን መተንተን ላይ ነው።

### *1.1 የጥናቱ ዳራ*

አጥኝዋ ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ እንድትሰራ ያነሳሳት ምክንያት በፍቅር ስም ልቦለድ የባእድ አምልኮ አስከፊነትን አና በየትኛውም አጋጣሚ ሆነ ቦታ ሰዎች የተለያየ ሀይማኖት እና አስተሳሰብ ኖሯቸው አንድ ላይ ተቻችለው መኖራቸውን ስለሚያሳይ በተጨማሪም ሁሉም ሰው አችላለሁ ብሎ ካመነ ምንም ነገር ከማድረግ ምንም እንደማያግደው ስለሚያሳይ ነው።

### *1.2 የጥናቱ አላማ*

- በፍቅር ስም የተሰኘውን ልቦለድ መፅሐፍ ከልቦለድ አላባዉያን አንፃር መተንተን
- በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሃፍን መተንተን እና ማሳወቅ።

### *1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ*

- ስለ በፍቅር ስም ልቦለድ ማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች ማሳወቅ።

-ተመሳሳይ ርዕስ ካላቸዉ ጥናታዊ ጽሑፍ ለሚሰሩ አጥኝዎች እንደ መረጃ ምንጭነት ያገለግላል ።

## *1.4 የጥናቱ ወሰን*

ይህ ጥናታዊ ፅሑፍ በፍቅር ስም የተባለዉን ልቦለድ መፅሐፍ ከልቦለድ አላባዉያን አንፃር የሚፈትሽ ሲሆን ይህም ሲባል ገፀባሕርያት አሳሳል መቼት ፣ ሴራ፣ ግጭትና ቃለ ተዉኔት አጠቃቀም ምን እንደሚመስል ትንተና ላይ የተወሰነ ነው።

## *1.5 የጥናቱ ዘዴ*

-አጥኝዋ ይሄን ጥናታዊ ፅሑፍ ስታጠና የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅማለች

አጥኝዋ ገላጭ የአጠናን ዘዴን ተጠቅማለች እና ከዚህ እርሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አጋዥ መፅሐፍትን በማንበብ በፍቅር  ስም ልቦለድ መፅሐፍትንም በተደጋጋሚ በማንበብ ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አጋዥ የሆኑ መፅሐፍትን እንደጥናቱ ዘዴ ተጠቅማለች ።

## *1.6 ጥናቱ የሚያሳቸዉ ጥያቄዎች*

ይህ ጥናተዊ ፅሁፍ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

- በፍቅር ስም የተሰኘዉ መፅሐፍ ገፀ ባህሪያት  አሳሳል ምን ይመስላል ?

-በፍቅር ስም የተሰኘው መጽሐፍ ሴራዉ ምን ይመስላል ?

- በፍቅር ስም የተሰኘው መፅሐፍ መቼት ምንድነው ?

- በፍቅር ስም የተሰኘው መፅሐፍ ግጭትና ቃለተዉኔት አጠቃቀም ምን ይመስላል ?

## *1.7 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች*

* አጥኝዋ ይሄን ጥናታዊ ፅሁፍ ስትሰራ ያጋጠሟት ችግሮች

- ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ የሚሆኑ በቂ የሆኑ አጋዥ መፅሐፍትን አለማግት።

- በዚህ ተመሳሳይ ርዕስ የተሰሩ ጥናታዊ ፅሁፍ አለማግኘት ።

- በቂ የሆነ ጊዜና ቦታ አለማግት የተለያዩ መረጃዎችን የማግኘት ችግር ።

## *1.8 የመፍትሔ ሐሳብ*

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ላይ አጥኝዋ የመፍትሔ ሀሳብ ብላ ያሰበቻቸው

- በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ተቀራራቢ የሆኑ ፅሁፎችን በመጠቀም ።
- በቅርቡ የሚገኙ አጋዥ መፅሃፍት በመጠቀም ።
- የለ እረፍት ቀንም ማታም ቁጭ ብላ በመስራት ።

## *1.9 የጥናቱ አወቃቀር*

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በአራት ምዕራፎች ተከፍሏል ። በምዕራፍ አንድ ላይ መግቢያ ፣ የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ ንዑስ አላማ ፣ የጥነቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ ወሰን ፣ የጥናቱ ዘዴ ፣ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ፣በጥናቱ ወቅት የጋጠሙ ችግሮች ፣ የመፍትሔ ሀሳብ ፣ የጥናቱ አወቃቀር ያካትታል ። በምዕራፍ ሁለት የልቦለድ ምንነት ፣የልቦለድ አላባውያን ፣የልቦለድ አይነቶች፣ የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ሲይዝ በምዕራፍ ሶስት ደግሞ በፍቅር ስም ልቦለድ አጭር ታሪክን እና ከልቦለድ አላባዉያን አንፃር መተንተንን ይይዛል ። በምዕራፍ አራት ደግሞ ማጠቃለያ አና ዋቢ መፅሐፍትን ይይዛል ።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2 ክለሳ ድርሳናት

### *2.1 የልቦለድ ምንነት*

ልቦለድ በዉኑ አለም የሚንቀሳቀሱትን የግለሰብና የማህበረሰብ ህይወት በቃላት አማካኝነት የሚያንጸባርቅ ምናባዊ ስዕል ሆኖ የሚታይ ዘርፍ ነዉ ።ልቦለድ በማህበራዊ ህይወት ዉጣዉረድ ዉስጥ የሚጋጥሙንን ዉስብስብ ጉዳዮች ክንውኖች በተወሰኑ ገፀባህርያት አማካኝነት አስመስሎ ማቅረብን የሚያጠቃልል ነው ። ዘሪሁን አስፋው "የስነፅሁፍ መሰረታዉያን"በሚለው መፅሐፍ ልቦለደን አንዲህ ይገልፀዋል ።

> ልቦለድ ማለት ማህበራዊ ህይወትን በስፋት በሚጥምና በሚስብ ዘይቤ በማሳየት አቅም ያለው የሰውን ልጅ አያሌ ገጠመኞች ማቅረብ የሚችል ኪነጥበባዊ ቅርፅ ነው ።ከሌሎች የስነፅሁፍ ዘሮች የበለጠ ዘላቂነትያላቸው የተስፋፋና የበለፀጉ የሰዎችን ምስሎች የመያዝ አቅም አለው ።በልቦለድ የሰዉ ልጅ ሃዘንናደስታጥላቻና ፍቅር ምኞትና ፍላጎት ብልፅግና ና ዉድቀት ባጠቃላይ ግብሩና አተያዩ በኪነታዊ ቋንቋ በሚቀርብለት ጊዜየራሱን አመለካከት በመመርኮዝ ነው ብለዋል ።(2005-152)

እንደ ዘሪሁን አስፋው አገላለፅ ልቦለድ ሕይወትን በተለይም የሠው ልጆችን ማህበራዊ ህይወት በዉብ ቋንቋ እና ለዛ የሚያቀርብ አንዱ የስነፅሁፍ ዘረፍ ነዉ።ታሪኩ ፈንታየ 'አማረኛ ሀሉ ለሁሉ' በሚለው መፅሃፉ ላይ ስለ ልቦለድ እንዲህ ብሏል።" ልቦለድ በዉኑ አለም የሚንቀሳቀሱትን የግለሰብና የማህበረሰብ ሕይወት በቃላት አማካኝነት የሚያንፀባርቅ ምናባዊ ስዕል ሆኖ የሚታይ ዘርፍ ነው ።ልቦለድ በማህበራዊ ህይወት ዉጣውረድ ዉስጥ የሚያጋጥሙትን ዉስብስብ ጉዳዮች ና ክንውኖችን በተወሰኑ ገፀባሕርያት አማካኝነት አስመስሎ ማቅረብን የሚያጠቃልል ነው። በልቦለድ ፅሑፍ ውስጥ የሚከናወኑ ድርጊቶች ማስረጃ የሚቀርባቸው የቁም አዉነቶች ባይሆኑም የተደረጉ በመደረግ ላይ ያሉ ናቸዉ ።(2011-110)"ልቦለድ ማለት ከቃሉ እንደምንረዳው በልብ ወለድ የተወለደ ወይም በልብ ዉሰጥ የተፈጠረ ማለት ሲሆን ደራሲው በእውነተኛ አለም ከሚያየዉ እዉነተኛ ርዕሰ ጉዳዮች በመነሳት በራሱ የሚፈጥረው ታሪክ ሂደት ነው ።

## *2.2 የልቦለድ አላባዉያን*

የልቦለድ አላባዉያን የምንላቸው አንድን ልቦለድ ልቦለድ ከሚያስብሉት ዉስጥ የልቦለድ አላባዉያን ይጠቀሳሉ ።ልቦለድ የተለያዩ አላባዎች ስብጥር ነዉ ።የልቦለድ አላባዎች ሰባት ናቸው ።አንደኛው ከጓደለ የልቦለድ ዉበቱን ያሳጣዋል ።ዘሪሁን አስፋው' የስነፅሁፍ መሰረታዉያን'በሚለዉ መፅሃፍ እነዲህ ብሏል ።

የልቦለድ ፍሬ ነገሮች ወይም አላባዉያን የሚታወቁት ታሪክ,ትልም,ገፀባህርይ ,መቼት ጭብጥ እና አንፃር ናቸው ።እነዚህ ለአጠናን እንዲያመች ተለያይተው ተጠሩ እንጂ በልቦለድ ዉስጥ በተናጥል ወገን ለይተው ለየብቻቸ የሚገኙ አይደሉም ።ስለ ታሪክ ሲወሳ ገፀባሕርያት መጠራታቸው አይቀርም ።ምክንያቱም ታሪኩ የገፀባህረያቱ ነውና ።ታሪኩን ጠርቶ ባለታሪኮችን መተው እንዴት ይቻላል? የገፀባህሪየቱ ታሪክ የሚፈፀመዉ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ ነው።(2005-154)ዘሪሁን አስፋው እንዳለው የልቦለድ አላባዉየን አንዱ ለአንዱ አስፈላጊ እና መሰረታዊ ነገሮችም ናቸው ።ለልቦለድ የልቦለድ አላባዉያን የምንላቸው የልቦለድ የጀርባ አጥንት ናቸዉ ።

### **2.2.1ታሪክ**

ታሪክ ለልቦለድ ቀዳሚዉ ነገር ነው ።ታሪኩ ከሌለ ልቦለድ ሊባል አይችልም ።ምክንያቱም አንድን ልቦለድ ልቦለድሊያስብሉ ከሚችሉ ነገሮች መሀል ቀዳሚወና ዋነኛው ታሪክ ነው።ታሪክ ለልቦለድ በጣም አስፈላጊ ነው ።ታሪክ ከሌለ ልቦለዱም የለም ማለት ነው ። ታሪኩ ፈንታየ 'የአማርኛ ሁሉ ለሁሉ 'በሚለዉ መፀሐፉ እንደተናገረው ።

ታሪክ በልቦለድ ዉስጥ ዋናና ሁሉን አቀፍ መሠረተዊ ነገር በመሆኑ ከላይ የተጠቀሱትን አላባዉያን

ሁሉ በዉሰጡ ያካትታል ።አድማጮችም ቅድሚያ ሰጥተው የሚናገሩት ስለ ታሪኩ አጠቃላይ ሁኔታ ነው ።ታሪኩ አሳዛኝ አስደሳች አልያም የለየለት ደረቅና አሰልቺ ሊሆን ይችላል ።ዞሮ ዞሮ የድርጊቶች ተከታታይነት ተያያዥነት የተጠበቀ ሆኖ ተደራሲያን የታሪኩን ፍፃሜ ለማወቅ እንዲጓጉ ልብ የሚሰቀልና የመሳብ ሀይል ያለው መሆን ይኖርበታል።ታሪኩ መሳጭና አጓጊ ካልሆነ ተነባቢነቱ ዝቅተኛ ስለሚሆን ልቦለዱ ዋጋ ያጣል ።(2011-110-111)እንደ ታሪሪኩ ፈንታየ አገላለፅ ለአንድ ልቦለድ ታሪክ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ እና ለልቦለድ ቀዳሚው ነገር ተረክ ነው።

### 2.2. 2 ትልም

ትልም የልቦለድን የነገሮችን ቅደም ተከተል የምናገኝበት አንዱ አላባ ነዉ።መንግሥቱ ታደሠ' ሜጋ የአማርኛ ሁሉ ለሁሉ መፅሃፍ ላይ እንዳሰፈረው ።ፊሊፕ ስቶቪክ ትልምን በሚመለከት ካጋጠሙት የተለያዩ ሀሳቦች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ሞክሯል።

> ቁልፍ ነገር ታሪክ ግልጽ ድርጊት ቀመር አጽም ብልሃት ያንድ ትረካ ህልውና ምክንያት በአንድ ትረካ ሊባል የፈለገውን ጉዳይ የሚታላለፍበት መንገድ እየተባለ ብያኔ ተሰጥቶት እንደተገኘ በዚህም የተነሳ እሳቤውን ለመገን ዘብ ችግር እንዳያጋጥም አስፍረዉታል። በአንድ ትልም የሚከናወኑ ድርጊቶች ለደራሲው ዋነኛ አላማ ተገዥ በመሆን በምክንያት ዉጤት ግንኙነት ተከታትለው ተሳስረው ሲጓዙ አንድ ቀጠሮ መፍታት ወይም አንድ የሚያረካ ዉጤት ላይ መደረስ አለበት ።(2005-157-158)

ትልም ከልቦለድ እንደሌሎች አላባዎች በጣም አስፈላጊ ነ።ዝኒ ከማሁ 'የስነ ፅሁፍ መሠረታውያን 'ከሚለው መፅሐፍ እንዳሉት "ትልም የልቦለድ ምልልስ ነዉ።ልክ የሰዉ አጥንት ሌላውን አካሉን ደግፎ እንደሚይዘዉ በልቦለድም ሁሉን ነገር ደግፎ የሚይዘው ትልም ነው።"

### 2.2.3 ገፀ ባህሪ

ገፀባህርይ የምንላቸው በአንድ ልቦለድ ውስጥ አካላዊ ስነ ልቦናዊ እና ሌሎች ማንነት ተሰጥቷቸው የሚወከሉ ሰዎች ናቸው ።ገፀባህርይ በልቦለድ ዉስጥ መኖር አለባቸው ። ዘሪሁን አስፋው 'የስነፅሁፍ መሠረታውያን 'በሚለው መፅሐፍ ስለ ገፀባህርይ እንዲህ ብለዋል ።

> በአንድ ልቦለድ ዉስጥ የሚተረክ ታሪክ የማነው ?የሚል ጥያቄ ሲጠየቅ መልሱ በቀጥታ የነ እገሌ ታሪክ ነው የሚል ጥያቄ ይሆናል ።እነገሌ ተብለው የሚጠቀሱት የተለያዩ ባህሪያት የህይወት ገጾች ያሏቸው ሰዎች ናቸው። ለምሳሌ ፍቅር እስከ መቃብርን ታሪክ የማን ነዉ ተብለን ብንጠየቅ በቀዳሚነት የሚሠጠን መልስ የበዛብህ የሰብለወንጌል እንዲሁም የፊታውራሪ መሸሻ የሚል ነው ።እነዚህ ስማቸው የተጠራልን ሰዎች የልቦለድ ገፀባሕሪያት ናቸው ።ገፀባሕርያቱ በልቦለድ አለም ስጋ ለብሰው ባህሪ ተጓናፅፈዉ መጠሪያ ተሰጥቷቸው መኖሪያ ተበጅቶላቸው የሚንቀሳቀሱ የሚተነፍሱ የሚናገሩ የሚበሉ የሚጠጡ እንደዉኑ አለም ሰዎች የሚሞቱ ናቸው ።(2005-159)

እንደ ዘሪሁን አስፋዉ አገላለፅ ገፀባሕርያት የልቦለድ አለም ሰዎች ናቸው ።የእዉነተኛዉን አለም ሰዎች ባህሪ የተሸከሙ ናቸው ።

### 2.2.4 ግጭት

ግጭት ማለት በአንድ ልቦለድ ዉስጥ ያሉ ገፀባሕርያት የሚፈጥሩት አለመግባባት ወይም የሃሳብ መፈጨት ነዉ ።ግጭት ሊፈጠር የሚችል የሚፈጠርም ጭምር ነው ።ታሪኩ ፈንታየ 'አማረኛ ሁሉ ለሁሉ 'በሚለው መፅሐፍ ስለ ግጭት እንዲህ ብሏል።

> ገፀባሕርያት በተለያዩ ምክንያቶች በመካከላቸው አለመግባባት ይፈጠራል ቅራኔ ዉስጥ ይገባሉ። ይህ ቅራኔ ንትርክን ፍጭትን ወይም ፍልሚያን ሊያስከትል ይችላል ።ግጭት የአንድ ልቦለድ ጽሁፍ የደም ስር ነው።በእንሰት ህይወት ዉስጥ የደም ስር ደምን ወደ ሰዉነት ክፍሎች ካልረጨ ሂወት የለም ።በዚሁ መልክ የልቦለድ ታሪክ ወደፊት ሊራመድ የሚችለው ተፃራሪ ኃይላት በሚፈጥሯቸው ግብግብ አማካኝነት በመሆኑ ግጭት ከሌለ ልቦለድ የለም ማለት ነው ።ግጭት በሰዉና በሰው መካከል በተፈጥሮ መካከል እንዲሁም ከሰው ከማህበረሰብ ከራሱ ጋር ሊጋጭ ይችላል ።(2011-114)

እንደ ታሪኩ ፈንታየ አገላለፅ ግጭት ሊፈጠር የሚችል የሚፈጥርና በመጨረሻም መፍትሄ የሚያገኝ ነገር ነዉ።

### 2.2.5. መቼት

መቼት ማለት ድርጊት የሚካሄድበት ቦታ የተፈፀመበት ማለት ነው ።መቼት ቦታዎችን የሚገልጽ የልቦለድ አካል ነው ። ዘሪሁን አስፋው 'የስነፅሁፍ መሠረታዉያን 'በሚለዉ መፅሐፍ እንዲህ ገልፆታል ።

> የልቦለድ ገፀባሕርያት እንደ እዉኑ አለም ሰዎች የመኖሪያ አካባቢ አላቸው ።በልቦለድ አለማቸወ የሚንቀሳቀሱትን ታሪካቸዉን የሚፈፅሙት ደራሲው በፈጠረዉ የተወሰኑ አካባቢ ሲሆን የሚኖሩበትና ታሪካቸዉ የሚገልጽ ዉበት ታሪካዊ ጊዜ ወቅት እለትና ሰአትም ይኖርባቸዋል ።ይህ የገፀባህሪያት መገኛ ስፍራና ጊዜ ባንድነት መቼት ይባላል። መቼት ታሪኩ የተከናወነበት ገፀባህርያቱ የሚኖሩበት ወይም የኖሩበት የገጠር ወይም የከተማ አካባቢ ብቻም አይደለም ።አያሌ ነገሮችን

ይጨምራል ።ከገጠሩና ከከተማው ህይወታዊ እንቅስቃሴ ጋር ያሉትን የተለያዩ ሁኔታዎች አካቶ በመያዝም ዓዘ ብዙ ነዉ ።(2005-179)

## 2.2.6 ጭብጥ

ጭብጥ ማለት አንድ ልቦለድ ሊያስተላልፈዉ የፈለገውን መልእክት ወይም የያዘዉ ሀሳብ ጭብጥ ነው ። መንግሰቱ ታደሠ ሞላ'ሜጋ የአማርኛ ሰዋሰው 'መፅሐፍ ላይ እንደሰፈረ።"ይህ የልቦፍሬ ነገር የታሪኩ መልዕክት በመባል ይታወቃል ።ደራሲዉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ታሪኮችን ፈጥሮ ገፀባሕርያትን በተለያዩ ግንኙነቶች ዉስጥ አስገብቶ ልቦለዱን ሲያዋቅር መነሻዉና ማእከላዊዉ ነገር ለሰው ልጆች የሚያስተላልፈው ቁም ነገር ጭብጥ እንለዋለን" ።(2009-71)

ጭብጥን ታሪኩ ፈንታየ 'የአማርኛ ሁሉ ለሁሉ ' በሚለዉ መፅሐፍ እንዲህ ሲል ገልፆታል።

> ማንኛውም ፅሁፍ ያለ አላማ አይፃፍም ደራሲው በሕብረተሰቡ ዉስጥ ያሰበውን የተገነዘበዉን ጉዳይ አስመልክቶ መሻሻል መለወጥ መቀበል አሊያም ሙሉ በሙሉ መወገድ የሚገባቸውን ለማመልከት በአላማ ተነስቶ ይፅፋል ።ይህ እንደተላለፍ የተፈለገዉ የደራሲው አላማ ጭብጥ ወይም ፍሬ ነገር ይባላል ።ጭብጦች አብይ እና ንዑስ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ።ዓብይ ጭብጥ ለዋናው ታሪክ መተረክ መተረክ ምክንያት የሆነን በአጠቃላይ ሁኔታና እንቅስቃሴ ተጨምቆ የሚወጣ ሲሆን እሱን አግዝፈው ለማዉጣት ከሚንቀሳቀሱት ገፀ ባህሪያት ህይወት የምቀስመዉ ቁም ነገር ደግሞ ንዑስ ጭብጥ ይባላል ።(2011-116)

ጭብጥ ደራሲው ሊያስተላልፈዉ የፈለገዉ መልክት ወይም ፍሬ ሀሳብ ሆኖ በልቦለድ ዉስጥ እንደ ታሪክ ገፀባሕርያት እና ሌሎችም ጭብጥም አስፈላጊ ነወ ።አንድ ልቦለድ ጭብጥ ከሌለዉ ልቦለዱ ተቀባይነት አይኖረውም ወይም በአንባቢያን ዘንድ ተወዳጅነት አይኖረውም ።እንደ ታሪኩ ፈንታየ አገላለፅ ጭብጥ ደራሲው ሊያስተላልፈዉ የፈለገዉ መልእክት ነው ።

## 2.2.7. አንፃር

አንፃር ማለት በአንድ ልቦለድ ዉስጥ እንደሌሎች የልቦለድ አላባዉያን አስፈላጊ ሲሆን በአንድ ልቦለድ ዉስጥ ታሪኩን የሚቸርክልን ጭምር ነው ። ዘሪሁን አስፋዉ 'በስነፅሁፍ መሠረታዉያን'በሚለው መፅሐፍ ላይ አንፃርን እንዲህ አስፍሯል ።

> ማንኛውም ልቦለድ በደራሲውና በአንባቢዉ መካከል ሆኖ ሁነቶችን የሚገልጽ የሚተረጉም አልፎ አልፎ በግልፅ አብዛኛውን ጊዜ ግን በዉስጠ ታዋቂ የሚኖሩ የታሪኩ ሂደት እየተከተለ የሚቀርብ ተራኪ አለዉ ተራኪው ታሪኩ የሚመለከተው ተሳታፊ ወይም ታሪክ የማይመለከተው ታዛቢ ሊሆን ይችላል።ተሳታፊ ከሆነ ተሪክ የሱም ተሪክ በመሆኑ የራሱንም ሆነ ከሱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ገፀባሕርያት ታሪክ በሰው አመለካከት ይቀርባል ።ታዛቢ ከሆነ ደግሞ ያየውን እና የታዘበዉን እንዳለ ነው የሚያቀርበው ።አንፃር ታሪኩን የሚተርከው ማን ነዉ ከታሪኩስ ጋር ያለው ግንኙነት ምንድን ነዉ ።ታሪኩ የተተረከዉ ከማን አኳያ ነው ሚለዉን መልስ ይሠጣል ።(2005 -190)

እንደ ዘሪሁን አስፋው ገለፃ አንፃር ታሪኩን የሚተርከው ማን ነው ከታሪከስ ጋር ያለው ግንኘነት ሚለዉን ጠቅሷል።

### 2.2.8. የልቦለድ አይነቶች

የልቦለድ አይነቶች ሁለት ናቸው ። እነሱም ረዥም ልቦለድ ናቸው ።አጭር ልቦለድ ከስነፅሁፍዘርፍ የሚመደብ ሲሆን እንደማንኛውም የፈጠራ ስራ የሰው ልጅን የህይወት ገጠመኞች እና ዉጣዉረዶች ከሽኖ እና አስዉቦ ያቀርባል ። ነገር ግን እንደ ረጅም ልቦለድ ሰፊ ቦታና የተለያዩ መልእክቶችን የሚያስተላልፍ አቅም የለዉም ።አጭር ልቦለድ አንድ ነጠላ ዉጤት ያለው በታሪኩ ዉስጥ ጥቂት ገፀባህርያት የሚንቀሳቀሱበት በቦታና በጊዜ የተመጠነ ጠባቃ ግጭት ያለው ቋንቋው በጣም ቁጥብ እንዲሁም አሻሚነት የሌለው እና በአንድ ቁጭታ ተነቦ የሚያልቅ የደራሲው ምናባዊ ፈጠራ ነው ። ረጅም ልቦለድ ሰፊ ቦታንና የተለያዩ መልክቶችን የሚያስተላልፍ ነው ። ረጅም ልቦለድ ያልተመጠነ እና ብዙ ሀሳብ ብዙ ገፀባሕርያትን የያዘው ጭምር ነው።ሀሳቡም ቁጥብ ሚባል አይደለም ።ደራሲው በምናቡ የሳላቸዉን ነገሮች ሰፋ ባለ ለሳብ የሚያቀርበው ረጅም ልቦለድ ነዉ ።ዘሪሁን አስፋው 'የስነፅሁፍ መሠረታዉያን 'በሚለው መፅሐፍ ስለ አጭር ልቦለድ እዲህ ብሏል ። ”የአጭር ዋነኛ ባህሪያት ጥድፊያ ነዉ።የሚተረከዉ ታሪክ ብዙ ባይጠማዝ ቶሎ ቶሎ መተረክ አለበት።ትልሙና የተለያዩ ክፍሎቹ ፍሰታቸዉን ጠብቀው ዝርዝር ነገር ሳያበዙ የተስፋፋ የመቼት

ገለጻ የገፀባህሪ ዳራ ሳይሰጥ በፍጥነት መጓዝ አለባቸው ። ቁጥብነት ነው ።ቁጥብነት በዋናነት በአጭር ልቦለድ አላባዉያን አኗኗር  እርስ በርሰ በሚፈጠሩት አይቀሬ ቅንጅት ዉሰጥ የሚታይ ነዉ ።(2005-230)"

## *2.3 የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት*

አጥኝዋ ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር የተሻለ ቅርበት ያላቸው በርካታ ጥናታዊ ፅሁፎችን ማግኘት ባትችልም ያገኘችቻቸውን ጥናታዊ ፅሁፎች አንድነት እና ልዩነት እንደናሙናነት ታቀርባለች ።በሰላማዊት ወርቁ በ2010 አ.ም በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥባት ትምህርት ክፍል " ባችለር ኦፍ አርትስ " ዲግሪ ማሟያ " ተፈጥሯዊነት በትኩሳት አስረጅነት" በሚል ስራ የተሰራ ጥናታዊ ፅሁፍ ነው ። ጥናታዊ ፅሁፉ በአራት ምዕራፎች የተዋቀረ ሲሆን በምዕራፍ አንድ መግቢያ የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ አላማ ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ ፣ የጥናቱ መጠነ ርዕይ ፣ የጥናቱ የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ፣ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና የመፍትሄ ሀሳቦች ፣ በምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ፣ ንድፈ ሀሳባዊ ቅኝት ፣ የልቦለድ አላባውያን ፣ የልቦለድ አፃፃፍ ስልቶች የያዘ ነው። በምዕራፍ ሰስት የደራሲያን እና ጋዜጠኛ ስብሃት ገብረ እግዚአብሔር አጭር የሂወት ታሪክ ፣ የትኩሳት ልበለድ ጭምቅ ታሪክ ፣የትኩሳት ልቦለድ ከአላባውያን አንፃር ፣ የትኩሳት ልቦለድ ከተፈጥሮአዊነት አንፃር ናቸዉ ። ምዕራፍ አራት ላይ  ደግሞ ማጠቃለያ ፣ ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው ፣ ዋቢ መፅሐፍትን ያካተተ ሲሆን የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ እና የሰላማዊት ወርቁ ጥናታዊ ፅሁፎች መግቢያ እና በምዕራፍ ሁለት የሚያነሷቸው ሀሳቦች ስለ ልቦለድና አላባውያን ይተነትናሉ ። ሁለቱም ጥናታዊ ፅሁፎች በአራት ምዕራፎች የተዋቀሩ ናቸው ። ሁለቱም ከረጅም ልቦለድ የተሰሩ ጥናታዊ ፅሁፎች ናቸው  ። የሁለቱ ጥናታዊ ፅሁፎች ልዩነት ደግሞ የህ ጥናታዊ ፅሁፍ "በፍቅር ስም" የተባለውን ልቦለድ መፅሐፍ ከልቦለድ አላባውያን አንፃር መተንተን ሲሆን የሰላማዊት ወርቁ ጥናታዊ ፅሁፍ ደግሞ " ትኩሳት" መፅሐፍን ከተፈጥሮአዊነት የልቦለድ አፃፃፍ ስልት አንፃር ይተነትናል ።

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.1. በፍቅር ስም ልቦለድ መጽሐፍ አጭር ታሪክ

ታለሰዉ በሰባት ሴት ልጆች ተከቦ ያደገ ልጅ ነዉ። ቤተሰቦቹ ስድስት ሴት ልጆች ከወለዱ በኋላ ወንድልጅ ለማግኘት ካላቸዉ ጉጉት የተነሳ ሰባተኛ ሆኖ ታለሰዉ ተወለደ በዚህ የተደሰቱት ቤተሰቦቹ ሌላ ወንድ ልጅ መዉለድ ቢፈልጉም የሱ ታናሽ ሌላኛዋ ሴት ተወለደች ሌላ ወንድ ልጅ እንደማይወልዱ ካወቁ በኋላ የታለሰዉ እናት አሱን ይባርከው እንደ አባቱ ጨቅጫቃ አይሁን አለች ። ታለሰዉ በልጅነቱ በጣም ይታመም ነበር እናትየዉ እሱን ለማዳን የተለያዩ ቦታዎች ትወስደዉ ነበር። የታለሰዉ እናት አና አባት ተለያይተው ነዉ ሚኖሩት የታለሰው አባት መታረቅ ቢፈልግም እናትየው ግን መታረቅ አልፈለገችም ። የታለሰዉ አባት መጠጥ የሚያዘወትር ሰካራም ነዉ ። ቤት ዉስጥ እርስ በእርሳቸው አይስማሙም ሁሉም ግን ለታለሰዉ ፍቅር ነበራቸው ። ቻይና ከተባለችው የሱ ታላቅ ዉጪ ቻይና ታለሰዉ ከመወለዱ በፊት እንደወንድ ትታይ ስለነበር በታለሰዉ ትናደድበት ነበር ። አንደኛዋ የታለሰዉ እህት ከነሱ የተለየ ሀይማኖት ተከታይ ናት ። የነ ታለሰዉ ቤት በጣም ጠባብ ነች ዝቅተኛ የኑሮ ጀረጃ ያላቸው ሰዎች ናቸዉ ። የታለሰዉ እናት ጉልት ገበያ እየሰራች ቤተሰቡን የምታስተዳድር ሲሆን አባትየው ደሞ የመንግስት ጡረተኛ ነዉ። ከቤታቸው ፊት ለፊት ደሞ ቹቹና እናቱ አንድ ጉስቁል ካለች ቤት ዉስጥ ይኖራሉ ።የቹቹ እናት በጣም ቀዥቃዣ ነች ቹቹ ደሞ የሀይምሮ በሽተኛ። የታለ የታለሰዉ እናት የተለያዩ ዶሮዎችን እየገዛች ለታለሰዉ ጤና እያዞረች በመጥፎ አምልኮ የምትጥላቸዉን ዶሮዎች ቹቹ እና እናቱ እየሰሩ ይበሉ ነበር። በዚህም ታለሰዉ ወደ ቹቹ ቀርቦ ቹቹን ማናገር ይፈልጋል ። አናትየዉ ግን እንዳይሄድ ትቆጣዉ ነበር ። ሲፈን ከናዝሬት ለሦሥት ክረምት ወደ አባቷ አቶ ተገኜ የመጣች የታለሰዉ ታናሽ የአበዛች ጓደኛ ነች።አበዛች ብዙም ተጫዋች ስላልሆነች ከሷ ይልቅ ከእናትየው ጋር ትግባባ ነበር ። ሲፈን የዋህ ተጫዋች ደስ የምትል ልጅ ናት ። ታለሰዉ ሲፈንን መግባባት ይፈለጋል ስምሽ እንዴት ወጣልሽ ብሎ ጠየቃት አላውቅም አለችዉ የሷ ስም እንዴት እንደወጣላት ለማወቅ መፅሐፍ ቅዱስ ማንበብ ጀመረ ። ልቦናው ደስ የሚል መልሰ ሰጠው የሷ ስም ትርጉም የማይገባ ብዙ ትርጉም አለው ።መፅሐፍ ቅዱስ ላይ የዋሆች ብፁሃን ናቸዉ ምድርን ይወርሳሉና ሚል ነበር ።የዋህ መሆን ሲፈን ላይ ይታይባት ነበር ብፁሃን ናት ብሎ አሰበ ግን ብፁሀን ምን እንደሆነ አላወቀም ። ለራሱ እስኪገርመዉ ድረስ ሲፈንን በጣም ወደዳት ። ታለሰዉ አይናፋርና የሴት አይነት ባህሪ ያለው ልጅ ነዉ ። ወንዳወንድ ሣይሆን እንደሴት አይነት ባህሪ ነዉ ያለው ። ሲፈን ደግሞ ይሄ ባህሪውን አሎደደችዉም ። ግን ቀስ በቀስ እየተግባቡ ሄዱ በጣም መቀራረብ

ጀመሩ ።ቻይና ባህሪውን እንዲቀይር ጥረት እያደረገች እያለ በመሀል አባትየው ወደ ዉትድርና ተመልሶ ስለነበር ሞቷል ተብሎ መርዶ መጣላቸው ። ሲፈን ወደ ናዝሬት ሄዳ ነበር ።ለለቅሶ ተመልሳ መጣች ታለ የሲፈን ፍቅር እየጨመረበት መጣ ለማግባትም አሰበ በዚህ መሀል በደረሰ የቦንብ ፍንዳታ ቻይና ሂወቷ አለፈ ። ቤተሰቡ በጣም አዘነ ቻይና እንደወጣች ነበር የቀረችው አስከሬኗ አልመጣም ። ከትንሽ ጊዜ በኋላም ታለሰዉ ከቤት በር ቆሞ እያለ ሦስት ወታደሮች ያያል ። ከሦስቱ አንዱ የታለሰዉ አባት ነበር ። የታለሰዉ አባት በመርዶ አርጅ እንሞተ ነበር የተነገራቸው እንጂ አልቀበሩትም ። የዛን ሰሞን ሲፈን ወደ ቤት ሄዳ ነበር ተመልሳ መጣች ቻይና መሞቷን አባትየው እንዳይሰማ አለቻቸው ። ሲፈን ታለሰዉ መኝታ ቤት ገብታ አባትህን ለምን ሰላም አላልአዉም አለችው የአባትህ መምጣት አልገረመህም አለችው ። አዎ አልገረመኝም አላት ከተሞከረ ማይሳካ ነገር የለም አላት። ከጊዜ ወደ ጊዜ ከሲፈን ጋር አብረው ከመዋል አልፈው ማደር ጀመሩ ሲፈን አረገዘች ። ሲፈን ሲፈን ልጅ ማየት ብትፈልግም አልቻለችም ሲፈን ሞተች ታለሰዉ አልረጋጋ አለ ሲፈንን በጣም ያፈቅራት ነበር ። ከትንሽ ጊዜ በኅላ ከቤታቸዉ ፊት ለፊት ያለው ቹቹ እናቱ ጥላዉ ጠፋች ወደነ ታለሰዉ ቤት ወሰዱት የታለሰዉ እናት ቹቹን አሳዳጊ የለዉም ብላ ለእርዳታ ድርጅት እንዲሰጥ አደረገች ። ታለሰዉ በፀና ታመመ እራሱን አላዉቅ እስኪል ድረስ ከፀበልና ከቃልቻ በኋላ ወደ ስነልቦና አምሮ ሀኪም ተወሰደ ሲጠይቁት ቹቹ ነኝ ነበር ሚለው ።ሀኪሞቹ ቹቹ የተባለውን ሰዉ እንዲያመጡት ነገሮቸዉ ። ቹቹ ወላጅ የለዉም ተብሎ ስለተወሰደ ማስመለስ ከባድ ነበር።ቢሆንም ግን የታለሰዉ እናት አለቃቅሳ አስመለሰቸው ። ቹቹ እንደመጣ ታለሰዉ ጤናዉ ተመለሰ ። ቹቹም የራሱን ታለሰዉም የራሱን ሂወት መኖር ጀመሩ ። ሂወት ብዙ ዉሽት አላት ለመዋሸት ከቤት የወጣ ሂወትን ሲያይ ተመልሶ ይገባል። (አለማየሁ ገላጋይ 2009)"በፍቅር ስም "

### 3.1. 1 በፍቅር ስም ልቦለድ ከታሪክ አንፃር

በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ በአንድ ቤተሰብ ዉስጥ ወንድ ልጅ ለማግኘት ገፀ ባህሪ ለቤተሰቡ ብቸኛ ወንድ ልጅ ነው።እናቱና እህቶቹ እሱን ከሌሎች ልጆች በላይ የሚያደርጉትን እንክብካቤ እና እናቱ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለእሱ ጥሩ ነገር ያደረገች መስሏት ለእሱ የምታደርገውን የተለየ የባእድ አምልኮም ያሳየናል ። ታለሰዉ በሴት ተከቦ ማደጉን ይወደዋል። እና በገፅ 7 ላይ እንዲህ ይላል" በሴት የመከበብን ጥቅም የምናዉቀው እኔና ጠቢ ሰለሞን ነን ........ህይወቴን ሳስበው በሴቶች የተዋቀረ ፅድቅ ሆኖ ይታየኛል ። ከፅድቅ የሚገኘው ደስታ እንዳይጓልብኝ በዙሪያየ ሽር ብትን የሚሉ ሰባት ሴቶች አሉ "።

" አንተ?ታለሰው? ተነስ? ............."( እናቴ )

" ተይዉ ትንሽ ይተኛ "(የመጀመሪያ እህቴ)

"ይርበዋል ፤ ተነስቶ ይብላ " (የእሷ ተከታይ )

" እንቅልፍ ሲጠግብ አዉቆ ይነሳ የለ ?" (የተከታይ ተከታይ )

" እሱ ከተኛ መች ይርበዋል ?"  ይቀስቀስ "(እናቴ)

"  ይልቅ ስትቀሰቅሱት እራሱን  እንዳያመዉ " ( አራተኛ ተከታይ )

ቻይና የተባለችው ታላቅ እህቱ ባህሪውን እነሱ ዲቀይር ጥረት ታደርግለታለች በተለይ ሲፈንዳ  ከተባለችዉ የአቶ ተገኔ ልጅ ጋር መዋል ከጀመረ በኋላ  ብዙ ጥ ረቶችን ታደርግለታለች ። ሲፈን ባህሪዉን አቶድለትም ግን ቀስ በቀሰ እሱን ከነ ባህሪው  ትወደዋለች ።

### 3.1.2 በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ ከገፀባህሪየት አሳሳል አንፃር

ታለሰዉ ማህበራዊ ፦ያላገባ ፣ ተማሪ ፣ ከቤተሰቦቹ ጋር የሚኖርና በሴት እህቶቹ ተከቦ ስላደገ የሴት አይነት ባህሪ  ያለበት ለዚህም ምሳሌ በገፅ 22 ላይ ታለሰዉ እንዲህ  ይላል ።" ቻይና ሴታሴት ስትለኝ ጭንቅላቴ ውስጥ የሚመጣልኝ የእሷ ንፅፅር ነዉ ። ሰውነቷን በስፖርት ስላወደነች ፤ ካራቴ ስለምትማር ፤ ሜዳ ስለምትውል ፤ ስለምትደባደብ ፤ ቤተሰቡን ስለምታስጨንቅ ....... እኔ እነዚህን ሁሉ አላደርግም ። በተለይ ከቤት ውጪ ለአፍታ እንኳ ከቆየሁ ዋስትና አይሰማኝም ። ከጉድኳድ ውጭ እንደተገኘች አይጥ ለሁሉ ዱላ የተጋለጥኩ ይመስለኛል ። "

ሞራላዊ ፦ አዛኝ የሰዎችን መጎዳት የማይፈልግ ከአሱ እኩል ሰዎችን የሚዎድ ቀርቦ መርዳት የሚፈልግ ልጅ ነው ።

አካላዊ ፦ ወጣት እድሜው በግልፅ ያልተቀመጠ  ።

ስነልቦናዊ ፦ የሚራራ ፤ ለሰዎች  የሚያዝን ፤ ብዙ ጊዜውን መፅሐፍ በማንብ የሚያሳልፍ

ቹቹ ማህበራዊ ፦ ያልተማረ ብዙ መናገር የማይችል ከእናቱ ጋር የሚኖር ፣ የሀይምሮ ችግር ያለበት  ፣ ብዙ ጊዜዉን ከቤቱ በር ላይ ቁጭ ብሎ የሚያሳልፍ ። ለዚህም ማረጋገጫ በገፅ 26 ላይ ታለሰው እንዲህ ይላል

"ቹቹ ጅሎ እና እናቱ ከኛ ቤት ባሻገር እግር ከላጫት መንገድ ዳር ይኖራሉ ። ከጥቁር ጣውላ የተቀረፀች የምትመስለው እናቱ ጉጥ አይኗን እያጉረጠረጠች ቀስ አያለ ሚሄድ ልጇን በሯ ላይ እስክታስቀምጥ ብቻ እረጋ ትላለች። ቹቹ የናቱ ተቃራኒ በሽታ ለክፎታል ሲያወራ በጣም ቀስ ይላል።

ሞራላዊ ፦ የዋህ ምንም ነገር እንደሚጎዳዉና እንደሚጠቅመው የማያውቅ

አካላዊ ፦ በታለሰዉ የእድሜ ክልል ውስጥ  የሚገኝ ወፍራም ድቡልቡል ቅርፅ ያለው ።

ስነልቦናዊ ፦ የሀይምሮ ችግር የለበት

ሲፈን ማህበራዊ ፦ ከነታለሰው ቤት አካባቢ የምትኖር ለሦሥት ክረምት ከናዝሬት የመጣች የታለሰው አባት ጓቸኛ የአቶ ተገኔ ልጅ እና የታለሰዉ ፍቅረኛ ሰዎችን ለማስደሰት የምትጥር ተግባቢ ሳቂታ ።

ሞራላዊ  ፦ የዋህ በቀላሉ የምትጎዳ ለሰዎች የምትራራ። ይህንንም ያልኩበት ምክንያት በገፅ 53 ላይ እንዲህ ይላል ማዘንና የዋህ መሆን ......ሲፈን ላይ ስለሚታይ ብፁዓን ናት ስል አሰብኩ ።የሲፈን ፊት ሀዘን የረበበት ነው። ዘወትር ከንፈሯ ላይ የምታንጠለጥለው የሳቅ ፈርጥ አላት።

አካላዊ ፦ በእድሜ የታለሰው ታናሽ የአበዛች ጓደኛ

ስነልቦናዊ ፦ ሰዎችን በቀላሉ የምትረዳ ፣ ለነገሮች ቅርብ የሆነች ንፁ ልብ ያላት ።

የታለሰው እናት ማህበራዊ  ፦ ነገዴ ፣ ደሀ ኑሮዋን ለማሸነፍ ደፋ ቀና የምትል ጠንካራ ሴት ናት ።

ሞራላዊ ፦ የዋህ ቁጡ

አካላዊ ፦ አካለዊ ሁኔታዋ በደንብ  ያልተገለፀ እድሜዋ በጎልማሶች አካባቢ የሚገኝ።

ስነልቦናዊ ፦ ለልጇ ስትል ብዙ ነገር የምትሆን

የታለሰው አባት ማህበራዊ  ፦ ወታደር ሆኖ ጡረታ የወጣ በሚያገኛት የጡረታ ብር የሚሰክር አብዛኛው ጊዜ ከባለቤቱ ጋር የሚጨቃጨቅ ቢሆንም ግን ነገሮችን ቶሎ የሚረሳ

ሞራላዊ ፦ የዋህ የዛሬን ብቻ የሚያስብ  እና ሀገሩን በጣም የሚወድ ለሀገሩም ብሎ ጥሮታ ከወጣ በኋላ ድጋሚ ወደጦርነት የዘመተ ጀግና ።

አካላዊ ፦ በደንብ ባይገለፅም ጥሮታ ስለወጣ እድሜዉ ጎልማሳ አካባቢ የወታደር አቋም ያለው

ስነ ልቦናዊ ፦ የዋህ የሀገር ፍቅር ያለበት  ሰዎችንም በእኩል አይን የሚያይ ጠንካራ አቋም ያለው ለዉሳኔ ቅርብ ።

ቻይና ማህበራዊ ፦ ዱርየ የምትባል  በራሷ መንገድ ነገሮችን ለማስተካከል የምትሞክር ወንዳወንድ ይሄንም የልኩበት ምክንያት በገፅ 15ላይ  " የወንድ አለባበስና የፀጉር አቆራረጥ አላት። የቤት ውስጥ ስራ አትሰራም ቻይና ካለች ማንንም አትፈራም  ።ማንንም  ሂሽ ትላለች ።"

ሞራላዊ ፦ የዋህ ለነገሮች የማትጨነቅ

አካላዊ ፦ወንዳወንድ እድሜዋ አልተገለፀም  የታለ ታላቅ እህት

ስነልቦናዊ  ፦ ሰዎችን መርዳት የምትፈልግ ሰዎችን ማገዝ የሚያስደስታት

በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ ብዙ ገፀባሕርያትን የያዘ ሲሆን የአብዛኛዎቹ ስም እና ማህበራዊ ሁኔታ በደንንብ ያልተገለጸ በመሆኑ በግልጽ የሚታዩትን አጥኚዋ ለመግለጽ ሞክራለች።

### 3.1.3 በ ፍቅር ስም ልቦለድ መጽሀፍ ከ መቼተ አንፃር

በፍቅር ስም ልብ ወለድ አጠቃላይ መቼት ኢትዮጲያ ውስጥ ውስን መቼት  አዲስ አበባ ከተማ በዋናነት ጠረታ ድልድይ ውስጥ የሚኖሩ የአንድ ቤተሰብ ሙሉ ታሪክ አካቶ በዋናነት   ግን ታለሰው በተባለው የቤተሰቡ ብቸኛ ወንድ  ልጅ ላይ ነዉ ። በዋናነት ጡረታ ድልድይ የነታለ መኖሪያ ቤት ውስጥ  ይሆንና ባለታሪኩ ታለ የትኛውም ስህተት የትኛውም ትክክል አልያም እውነት ወይም ውሸት ለማረጋገጥ  ባለመቻሉ ሁሉም ሰው በፍቅር ስም የሚኖር እውነት የላገኝ ውሸትን የሚኖር እውነት አየጠፋ እንደሆነ አግዝፎ ለማሳየት ችሏል። ጡረታ ድልድይ ጭር ያለ ቦታ ብርድና ሙቀት የሚፈራረቁበት ቦታ እና ከመንፈሳዊ እስከ ባዕድ አምልኮ የሚያመልኩበት ቦታም ነው። በታለ ታሪክ   ታለ ታዲያ እነዚህ ሰፈር ሲቆይ የናዝሬት  ልጅ የሆነችውን ከናዝሬት ለሶስት ክረምት በእንግድነት ወደ አባቷ አቶ ተገኔ የመጣችውን ሲፈንን አፍቅሮ ነዉ ።እና

በጎረቤታቸው ቹቹ ጤና ማጣትም ምክንያት ለሁለት ወር ያክል የጤና ችግር ደርሶበት ይታያል ። በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ የረጅም ልቦለድ መቼት ገለፃን በደንብ ያሟላ ነው። መቼቱንም በደንብ አብራርቶ ያሳያል ። የነታለሰው ቤት በጣም ጠባብ ነው ለዚህም ማረጋገጫ በገፅ 22 ላይ ታለሰው እንዲህ ይላል።" ቤታችን ሽንጣም ነው። በጭቃና በጨፈቃ የተዋቀረ አውቶብስ ይመስላል ። ዘወትር ታምር ገድል የሚሆንብኝ እዚህ ሞተሩ የወረደ ሰንካላ የአፈር መኪና ውስጥ አስር ሰው የመኖሩ ጉዳይ ነው። እኔ አባቴና ቻይና ቆጥ መሳይ የአጠና አልጋዎች ተሰልፈው ቤቱን ድንገተኛ ክፍል አስመስለውታል ።አልጋዎቹ ለቤቱ እንዲመቹ ተደርጐ በአናጢ የተዋቀሩ ናቸው።ከሶስታችን ውጪ እናቴን ጨምሮ ሴቶቹ የት፣ አንዴት እንዳደሩ ማወቅ አልችልም ። አምሽተው ይተኛሉ ። በማለዳ ይነሳሉ። ስገምት ሴቶቹ የሚተኙ እንደ አውቶብስ ተሳፋሪ በመደዳ ተቀምጠው ነው። ወይም መቀመጫ እንዳጣ የአውቶቡስ ተሳፋሪ የጣሪያውን ማገር በመያዝ ቆመው እየተወዛወዙ ያድሩይሆናል ።አላውቅም ። ይሁንና ቤታችን በሴቶቹ ወግ ወጉን ያያል ።ሳሎን፣መኝታ ቤት እና እቃ ቤት ተብሎ ተከፍሏል ።ሰቄ ይመጣል። ቤታችን በሀሳብ ተከፍላለች በአምሳል አንድ ነች ። የሳሎን፣ የመኝታ ቤትናየዕቃ ቤት ድንበር የፀናው እንደ ኬክሮስና ኬንትሮስ መስመር በሀሳብ እንጂ የቆመ ወይም የተጋረደ ነገር የለበትም ።አዚች የጭቃ አውቶብስ ውስጥ በኋላ ለገባ ተሳፋሪ በግምት እስከ ትኬት ቆራጪ ድረስ ሳሎን መሆኑ ነው ። በትኬት ቆራጪ እስከ መካከለኛው በር ድረስ መኝታ ቤት ሲሆን ከዚያ ወዲያ እስከ ሾፌሩ ዕቃ ቤት ነው። በኛ የጭቃ አውቶቡስ ተመስገን ተመስገን ከማለት አልፈን በሰፈርተኛው ላይ እንኩራራለን ። ምክንያቱም የአንዳንዱ ቤት ሚኒ ባስ ነዋ! ኧረ ሞተር ብስክሌት የሚያክልም ቤት አለ አሉ ። ባልና ሚስት አግዳሚ ወንበር ላይ ፊትና ኋላ ተፈናጠው ሲያድሩ እየታየኝ በእኛ ቤት ኩራቴን አፋፍሚያለሁ ። "

## 3.1.4. በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ ከጭብጥ አንፃር

በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ ብዙ ጭብጦችን ይዞ ብዙ ነገር ለማስተላለፍ የተሞከረበት ልቦለድ መፅሐፍ ነዉ ።በዚህ ታሪክ ጭብጥ በዛ ቤተሰብ ዉስጥ ያለውን የወንድ ልጅ ፍቅር ማሳየት እና እናቱ ለሱ ብላ ከሌሎች ልጆች በላይ ምታደርርግለትን የተለየ ፍቅርና እንክብካቤ ያሳየናል በተጨማሪም በዚህ ልቦለድ አበባ የተባለችው የታለሰው እህት ጴንጤ ናት እነሱ ደግሞ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ናቸዉ ።በአንድ ቤት ውስጥም ተቻችለው መኖራቸውን ያሳየናል ።ሌላው አጥዋ ጭብጥ ብላ የወሰደችው የዚህ ቤተሰብ ፍቅርን ነው ።ሁሉም የቤተሰቡ አባል የተለያየ ባህሪ ነው ያለው ። በዚህ ልቦለድ ውስጥ ሌላኛው አጥኝዋ ጭብጥ ብላ

የወሰደችው የባእድ አምልኮ አስከፊነት ነው። በገፅ 14 ላይ  ለማየት እንደሞከርነው "ልጄን አልተውም ከመላዕክት እስከ አጋንንት ደጅ የረገጥኩበትን ከአባ ኪሮስ እስከ ዲያቢሎስ ደጃፍ የ ተንበርከኩበትን እስላም ክርስቲያኑን ደጅ የጠናሁበትን ልጄን አልተውም ትላለች"። ጡረታ ድልድይ የተለያዩ ነገሮች ይካሄዳሉ ከባእድ አምልኮ አስከ መልዕክት ።ጡረታ ድልድይ ከዚህም በላይ ደግሞ ማህበራዊ ሂወት በደንብ የሚካሄድበትበደስታም በሀዘንም ሰዎች የሚገናኙበት በታም ጭምር ነው።

### 3.1.5 በፍቅር ስም ልቦለድ ከግጭት አንፃር

ግጭት በአንድ ረጅም ሆነ አጭር ልቦለድ ውስጥ የሚፈጠር አለመግባባት እንደሆነ  ይታወቃል ። ግጭት በልቦለድ አለምውስጥ የፍላጎት የሀሳብ አለመጣጣም  ያሳየናል ።ማለትም ፍላጎቶቻቸው ሳይጣጣም ሲቀር ሰዎች ከሰዎች ጋር ሰዎች ከራሳቸው ጋር  ሰዎች ከፈጣሪያቸው ጋር ይጋጫሉ ። ይህም ሲሆን ደግሞ አጥኝዋ የተመለከተችው ታሪክ ማለትም በፍቅር ስም ሰዎች ከሰዎች ጋር ሰዉ ከራሱ ጋር  ሲጋጭ እናያለን ግጭት የምንለው በአፍ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን በድርጊትም ሲገለፅ ነዉ ። በዚህ ልቦለድ ታለሰው የተባለው ገፀባህርይ ከራሱ ጋር ሲጋጭ እናያለን ከታላቅ እህቱ ከቻይና ጋር እና እናት እና አባቱ ሲጋጩ እናያለን ። በገፅ 18  ላይ የታለሰው አባት እንዲህ ይላል " ጠንቋይ እየቀለብኩ ጣ! የጠንቋይ ልጅ አያሳደኩ ! ይላል " ሶሻሊዝም ይባላል እዚህ ደሞ የጠንቋይ በዝባዥ በአደባባይ ይፋንናል ! " የታለሰው እናት ገፅ 19 "ኧረ  አንቱ ሰውዬ ተነኩ እንዴ ?......... በዚህ አመልዎ ነው ስጋው  ደሚ በቀሉስ ለመለከፍ ካልሆነ ..... አይ በቃ እንግዲህ " ታለ

ሰው ብዙ ጊዜም ከራሱ ጋር ሲጋጭ ነበር። በሴቶች ተከቦ ስላደገም የወንድ ልጅ ፀባይ ምን እንደሆነም አያዉቅም። የሆነ ነገር ሲያደርግ ይሄን ወንድ አያደርግም የሴቶች ባህሪ ነው እየለ ብዙ ነገሮችን እየተወ ከራሱ ጋር ይጣላል ። እና እናቱ የተለያዩ ባእድ አምልኮዎች እያደረገች  የሱን ሂወት ለማስተካከል የቹቹን ሂወት ስታበላሽ ሁሌም ያሳስበው ነበር ። ምንም ማድረግ ባለመቻሉም ከራሱ ጋር ይጣላ ነበር።

### 3.1.6 በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ ከትልም አንፃር

በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ የረጅም ልቦለድ ትልም ባህሪን የጠበቀ ነዉ ።  ማለትም ለታሪኩ መፈጠር ምክንያት የሆነው ሴራ የተወሳሰበ ነው እና የረጅም ልቦለድ ባህሪን ያሟላ ነው። አጥኝዋ ይህን ማለት የቻለችበት ምክንያት ለታሪኩ መፈጠር መሠረት የሆነው ሴራ የተወሳሰበ እናየረጅም ልቦለድን የሚገልጽ ነበር። ሊያስተላልፍ የፈለገው ግልጽ ድርጊት በደንብ ታይቷል ። የተለያዩ መልዕክቶች ማስተላለፍ ችሏል ።

ግልፅ ድርጊት ያለው ነበር ሊተላለፍ የተፈለገው መልዐክትም በደንብ ግልፅ ነበር ። ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ግልፅ ነው ያልንበት ምክንያት በገፅ 216 ላይ እንዲህ ይላል "ሂወት ከዚህ በላይ ታምር አላት ምን ሊደንቃት ? ካላመንክ ቁጭ ብለህ እንደዚህ በቀን አልማት ።ህልምህን ሰርቃ ጨምራ እና አሽሞንሙና አንድ ጥግ ውሽት እያጠጣች አፅድቃ የህልምህን ቅጠል ትውልድ ፍየል ሆኖ ሲቅመው ትደርሳለህ ።"

### 3.1.7. በፍቅር ስም ልቦለድ ከአንፃር ሲታይ

በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሐፍ የአብዛኛውን ሰው ስሜት እና ባህሪ ያጋጠማቸውን ነገር እና የተለያዩ ባህሪያቸው ታለሰው በተባለው ገፀባህርይ አማካኝነት ለማወቅ ችለናል ። በዚህ ልቦለድም የተለያዩ ነገሮች ለመዳሰስ ተሞክረዋል የተለያዩ ጭብጦች ግጭቶችም ተፈጥረዋል የተለያዩ ገፀባሕርያትም ተሳትፈዋል ሆኖም ታሪኩ በዋናነት የሚያጠነጥነው በታለሰው ሂወት ነው። በዚህ ልቦለድ ደራሲው የተደራሲያን ቀልብ ለመያዝ ሞክሯል ። የተለያዩ መልእክቶችንም አስተላልፏል አስተምሮበታል አጥኝዋ ለመረዳት እንደሞከረችው ይሄ ልቦለድ የሚተረከው ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በአብዛኛው ታለሰውበተባለው ገፀባህርይ ነው።ታለሰው በዚህ ልቦለድ ውስጥ ስለ ቤተሰቡም ሆነ ስለ ሲፈን ያወራ ነበር።ይህንንም ለማረጋገጥ በገፅ 180 ላይ ታለሰው ሰለ ቹቹ እንዲህ ይላል ።አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ስመለስ ቹቹ ገላውን ታጥቦ ደረስኩ ። ያጠቡት እህቶቼ ነበሩ ። ያላሰብኩት ስለነበር እጅግ አድርጎ ገረመኝ ።እንደመኪና ቧንቧ ላይ በተቀጠለ ጎማ ውሃ እየረጬ በቁም መጥረጊያ ሲያሹት በአይነ ህሊናየ ታየኝ።

# ምዕራፍ አራት

## 4 ማጠቃለያ

በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ በፍቅር ስም ልቦለድ መፅሃፍ ከልቦለድ አላባውያን አንፃር ተመልክቷል ። በዚህ ልቦለድ የሚያነሳቸው ታሪኮች ፣ ገፀባሕሪዎች ፣ድርጊቶች ለማህበረሰቡ የሚያስተላልፈው መልዕክት ዋነኛው የባዕድ አምልኮ አስከፊነት እና ቤተሰቡ ውስጥ ያለውን የወንድ ልጅ ፍቅር እና ሁለት አይነት ሀይማኖት እንዴት ተቻችለው አንድ ቤት ውስጥ መኖር መቻላቸውን በዝርዝር ተመልክቷል ።ሁሉ ሰው እችላለሁ ብሎ ከተነሳ ምንም ነገር ማድረግ እንደማያቅተውም አሳይቷል ።በፍቅር ስም ልቦለድ ብዙ መልዕክቶችን እና ሀሳቦችን አስተላልፏል ።በመጨረሻም በፍቅር ስም ልቦለድ ከልቦለድ አላባውያን አንፃር በዝርዝር ተመልክቷል ።

## ዋቢ መፅሐፍት

*መንግሥቱ ታደሠ ። 2009 ። "ሜጋ የአማርኛ ሰዋሰው "ሜጋ አሳታሚና አከፋፋይ ።*

*ታሪኩ ፈንታዬ ። 2011።"አማረኛ ሁሉ ለሁሉ" ። ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ ።*

*አለማየሁ ገላጋይ ። 2009። "በፍቅር ስም" ። አዲሰ አበባ ።*

*ዘሪሁን አስፋው ። 2005።" የስነ ፅሁፍ መሠረታውያን" ። በንግድ ማተሚያ ቤት አዲሰ አበባ ።*

*ዝኒ ከማሁ ። 2005 ። " የስነፅሁፍ መሰረታውያን"። በንግድ ማተሚያ ቤት ።*